# <u>የብአዴን 30ኛ ዓመት የምስረታ በዓል በኢትዮጵያና በዋሽንግተን ይከበራል</u>

የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ / ብአዴን / ቅዳሜ ፣ ኅዳር 11 ቀን 2003 ዓ.ም. ወይም እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 20/2010 የተመሠረተበትን 30ኛ ዓመት የልደት በዓሉን በደስታ ያከብራል:: ይህ የብአዴን 30ኛ የልደት በዓል፣ እንደ ኢሕአዴግ አባልነቱ ከትግል አጋሮቹ ጋር በመላው ኢትዮጵያና በሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዘንድ፣ በአክብሮትና በአድናቆት የሚዘከር ቢሆንም፣ በተለይ ድርጅቱ ታግሎ በአደራጀውና አደራጅቶም በአታገለው የአማራ ክልል ሕዝብ መካከል በከፍተኛ ድምቀትና የተሐድሶ መነሳሳት ስሜት እንደሚከበር ይታመናል::

የአማራው ክልል ሕዝብ ከብአዴን ጋር ወግኖ የከፈለው የትግል መስዋእትነት ብቻ ሳይሆን፣ በብኤዴን አመራር ለድል ከበቃ በኋላ፣ በአለፉት 20 ዓመታት የተቀዳጃቸው የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኀበራዊ ልማት ውጤቶች በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ሊያከናውን ከወጠናቸው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅዶች... ጋር፣ በልዩ የትግልና የመነሳሳት መንፈስ ለማክበር በርካታ መስናዶዎች እያደረገ ይገኛል:: በአጭሩ፣ ኅዳር 11 ቀን 2003፣ የአማራው ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ሕያው አካል ሆኖ፣ ሕዳሴዋ ሳያሰልስ እንዲቀጥል የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማበርከት ከራሱና ከትግል አጋሮቹ ጋር አዲስ ኪዳን እንደገና የሚገባበት ዕለት ይሆናል::

በተጨማሪ፣ ይህ የብአዴን 30ኛ የልደት በዓል፡ ኢትዮጵያውያንና የአማራው ብሔር ተወላጆች በአጠቃላይና፣ በተለይም የብአዴን ደጋፊዎችና አባላት በያሉበት እንዲያስቡትና እንዲሳተፉበት ጥሪ የተላለፈ በመሆኑ፣ በሰሜን አሜሪካና በተለያዩ ሀገሮችና ከተሞች እንደሚከበር ታውቋል::

ስለሆነም በዋሽንግተን ዲሲና አካባቢዋ የምንገኝ ኢትዮጰያውያን ፣ የብአዴን ደጋፊዎችና አባላት እንዲሁም የክልሉ ተወላጆች ከዚህ ጥሪ አንፃር የተለያዩ ዝግጅቶች መጀመራችንን ከወዲሁ እያስታወቅን በሚቀጥለት ተከታታይ ሳምንታት የምናደጋቸውን መግለጫዎችና ፕሮግራሞች በሬዲዮ፣ በኢንተርኔትና በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን እንድትከታተሉ እየጋበዝን ለምታደርጉልን ትብብር ሁሉ ከወዲሁ ከልብ እናመሰግናለን:: የልደት በዓሉ በዋሽንግተን የሚከበረው በኢትዮጵያ የሚከናወነው ከተጠናቀቀ በኋላ ቢሆንም፣ ዕለቱን፣ ሰዓቱንና ቦታውን ወደፊት የምናሳውቃችሁ ይሆናል::

ከበዓል አዘጋጅ ኮሚቴው::